የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ–የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5[th] Year No. 36
ADDIS ABABA - 9[th] February 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፶፮/፲፱፻፺፩ ዓ·ም·
ለብሔራዊ የከብት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............................ ገጽ ፱፻፹፫

CONTENTS

Proclamation No. 156/1999
African Development Fund Loan Agreement for financing the National Livestock Development Project Ratification Proclamation ............ Page 983

### አዋጅ ቁጥር ፻፶፮/፲፱፻፺፩

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለብሔራዊ የከብት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ዩ·ኤ· ፳፯ ሚሊዮን (ሃያ ሰባት ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ ኖቬምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የከብት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻፶፮/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 156/1999

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of UA 27,000,000 (twenty seven million Units of Account) for financing the National Livestock Development Project, was signed in Abidjan, on the 20[th] day of November 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 9[th] day of February 1999.

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows :

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for financing the National Livestock Development Project Ratification Proclamation No. 156/1999."

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·አ·አ ኖቬምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ኤፍ/ኢ·ቲኤች/ኤል ቪ ኤስ–ዲኢ ቪ ፺፰/፵፩ የብድር ስምምነት ነው።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ·ኤ· ፳፯ ሚሊዮን (ሃያ ሰባት ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ።

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. F/ETH/LVS–DEV/98/41, signed in Abidjan on the 20th day of November, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund .

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the loan amount of UA 27,000,000 (twenty seven million Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 9th day of Feburary, 1999.

Done at Addis Ababa, this 9th day of February, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE